# ባለህበት ሸፍት

ወያኔ ለባዕድ ፣ ወለል አርጎ በሩን

ሸነሸነ ሸጠው ፣ ለም መሬት ድንበሩን

ገበሬን ነቀሉት ፣ ለቆ ወጣ አገሩን

ሰብሉን ፣ በላው ባዕድ ፣ ህዝብ ሲግጥ አፈሩን

አልቀረለት ዛሬም ፣ ጦም ውሎ ማደሩን

ባልፈጸመው ወንጀል ፣ መጋዝ መታሰሩን

ቻይና ህንዱ ነግሶ ፣ እሱ መባረሩን

ባገሩ ተዋርዶ ፣ መረገጥ ማፈሩን

ተነስ አምፅ እንጂ ፣ አብቃ ማማረሩን

ያግርህን ጫካ ፣ ጋራ ሸንተረሩን

መቼ አጣኸውና ፣ መደበቂያ ዱሩን

ኑሮህን ታውቃለህ ፣ መች ትሻለህ  ምክሩን

ባለህበት ሸፍት ፣ አንሳውና ጦሩን

ደም ይነከር ሳንጃው ፣ የለመደ ግብሩን

ታውቅበት የለም ወይ ፣ ጠላትክን መምተሩን

ወላጁን እስኪረግም ፣ ጠልቶ መፈጠሩን

አሳድና በለው ፣ እራስ ቅል ግንባሩን

አገር ሻጭ ከሃዲው ፣ አያግማው መንደሩን

ዛሬ ነገ ሳትል ፣ አጣድፈህ ቀብሩን

ነጻ አውጣት አገርክን ፣ ከተማ ገጠሩን

ከጫንቃህ አውርደህ ፣ ሰባብረው ቀንበሩን

አጎናጽፈው ህዝቡን ፣ የናት ሀገር ክብሩን ።

ታዛቢው

February 2, 2010